# የሕዝብ ውክልና የሌለው መንግስት የሚፈርመው የክህደት ውል ተቀባይነት የለውም፣

የአንድ ሐገር ሕዝብ በታሪክ፣ በባልህና በስነልቦና የተቆራኘ ሲሆን፣ ይህንን መተሳሰር ሐገራዊ ትርጉም የሚኖረው ሉዑላዊነቱን ያስከበረበት ነፃ ግዛት ሲኖረው ነው። ይህም በመህኑ የነፃ ሉዑላዊ ግዛት ጥያቄ ዋናውን ቦታ ይዞ ይገኛል። ነገር ግን ዛሬ በሐገራችን የሥልጣን ኮርቻ ላይ ተፈናጦ የሚገኘው ዘረኛ አምባገነን ቡድን፣ ገና ከውልደቱ ጀምሮ የቆመበት መሰረት ዘረኝነት በመሆኑ፣ ምንም ሐገራዊ ጉዳይ የሚያሳስበው አለመሆኑን በተለያዩ ጊዚያት በወሰዳቸው ብሄራዊ ደህንነትንና ጥቅምን የመሸጥ ውሳኔዎቹ በበቂ ሁኔታ አስመስክሯል። ይህ ዘረኛ ቡድኑ ከስልጣን ከመውጣቱ በፊት በነበሩት አመታት በተለያዩ ድርጊቶቹ የዘረኝነትን ጠባብ ስሜቶች ሲያንጸባርቅ ቆይቷል።

በተለይ ለሥልጣን በበቃበት ጊዜና ከዚያም በኋላ፣ የዚህ ቡድን መሪ መለስ ዜናዊ በአደባባይ፣ "የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚባል ሕዝብ የለም፣ የተለያዩ የዘውግ ማሕበረሰባት እንጂ፣ ለወላይታው የአክሱም ሐውልት ምኑ ነው?፣ የኢትዮጵያ እድሜና ታሪኳ ከመቶ አመት አይበልጥም፣ እሱም ቢሆን የአንድ አካባቢ ታሪክ ነው፣ ለእኛ ባንዲራ ጨርቅ ነው፣ እዚህ የመጣነው ኢትዮጵያዊነትን ለመሞከር ነው፣ ካልተስማማን ደግሞ በህገ መንግስቱ ያስቀመጥነውን መብት ተጠቅመን ጥለን እንሄዳለን፣ የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ የሚያስጨንቀን ጉዳይ አይደለም፣" ሲሉ ተደምጠዋል። ዘረኝነት በአቶ መለስ ህሊና ላይ የነሰነሰው መረዝ ምን ያህል አደገኛ ደረጃ ላይ እንደ ደረስ ከዚህስ በላይ ምን ማስረጃ ማቅረብ ያስፈልጋል።

አቶ መለስ ዜናዊ ለሚመሩት የዘረኛ አምባገነን መንግስት፣ የሐገር ድንበር በወረቀት ላይ የተሳለ ተራ የጭረት መስመር ነው፣ ብሎ ስለሚያምን ፣ ሐገርን እና ሕዝብን ከመሪዎቹን ጋር የሚያስተሳስሩ የብሄራዊ ደህንነትና ጥቅም መሠረታዊ ውሎች፣ አለመከበራቸው ብዙም አይገርመንም ። ዘረኝነቱ ሐገራዊ ራዕይ እንዳይኖር ሲያደርግ ፣ በሥልጣንን በመጠቀም የሚካሄደው ይሉንታ ያጣ ዘረፋና እብሪት የአምባገነንነቱ በቂ ማስረጃ ነው።

ሰሞኑን በሰሜን ምእራብ እና በምእራብ የሐገራችን የሱዳን ድንበር ላይ ለተከሰተው አደገኛ ሁኔታ መእስዔ የሆነው "ውለታ" ችግሩ፣ ብሄራዊ ጥቅምና ደህንነትን አሳልፎ በመስጠት፣ የራስን ጠባብ ቡድን ጥቅም ለማስቀደም የተደረገ በመሆኑ ነው ። ከተለያዩ ምንጮች የሚደርሱን መረጃዎች የሚያመክቱትም ይህንኑ ነው። በልማት ሥም ከሰሜን ምዕራብ የሐገራችን ክፍል እየተመዘበረ በሱዳን በኩል ለውጭ ገበያ ተሸጦ በአውሮፓና አሜሪካ ባንኮች የሚከማቸው በዘረፋ የሚገኝ ጥቅም፣ በተሻለ ሁኔታ ለማካሄድ የተደረገ አሳፋሪ "ውለታ" መሆኑን ነው ። የሱዳን መንግስት ለዚህ የዝርፊያ ገበያ የሚያስፈልገውን አገልግሎት ያመቻቻል፣ በአንጻሩ በድንበራችን ላይ የፈለገውን መሬት ይወስዳል።

ይህ ድርጊት በአካባቢው ሕዝብ ላይ የህይወት አደጋ ፣ የንብረት ውድመት፣ እያስከተለ ነው። ብሄራዊ ድንበርን ማስከበር የአንድ መንግስት መሰረታዊ ግዴታ ቢሆንም፣ "የእኛ" መንግስት ከሌላው ወገን በመሰለፉ፣ ይህ ሀላፊነት፣ የሐገሩን ድንበር ለመከላከል በቁርጥኝነት በተነሳው የጎንደርና የአካባቢው ሕዝብ ትከሻ ላይ ወድቋል። ሕዝቡ በራሱ አነሳሽነት በሐገሩ ድንበር አካባቢ የሚደርሰውን ጥቃት ለመከላካል እየሞከረ ነው።



1Crowndale Road London NW1 1TU Tel/Fax: 020 7168 9893 E-mail: kinijit97@yahoo.co.uk

ይህም በመሆኑ በዩናይትድ ኪንግደም የምንገኝ የቅንጅት ድጋፍ ድርጅት አባሎችና ደጋፊዎች፣ እንዲሁም መላው ኢትዮጵያዊ ወገን:-

1. በሰሜን ምዕራብ እና በምዕራብ በሚገኘው የሐገራችን ደንበር አካባቢ የሚገኘው ወገናችን የሐገሩን ድንበር እና የራሱን መንደር ለአለማስደፈር የሚያደርገውን ተጋድሎ በሙሉ ልባችን እንደግፋለን ። በዚህም ወገናችን ላይ የሚደሰውን ጥቃት በአስቸኳይ እንዲቆም እንጠይቃለን።
2. በውጭ ሐገር የሚገኙ የቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶችና ሌሎችም ወገኖች ለጥቃት የተጋለጠውን ወገንኖቻችን ለመርዳት የሚቻልበትን ተግባራዊ እቅድ እንዲነደፍና በስችኳይ ሥራ ላይ እንዲውል፣ ለሌሎችም እህት ድርጅቶች ጥሪያችንን እያቀረብን በእኛ በኩል የድርሻችንን ለመወጣት ዝግጁነታችንን እንገልጻለን።
3. የሕዝብ ውክልና የሌለው ዘረኛ አምባገነን ቡድን በሐገር ደረጃ የሚፈርመው የክህደት ውል ህጋዊነት ስለማይኖረው ፣ የሱዳን መንግስት ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም በወገናችንና በሐገራችን ላይ የሚያደርሰውን ጥቃት፣ ለወደፊቱ በሁለቱ ሕዝቦችና መንግስታት መሀከል ሊያስከትል የሚችለውን መዘዝና ጠንቅ ተረድቶ ከእንዲህ አይነቱ ህገ ወጥ ውለታ እራሱን እንዲያገል አጥብቀን እንጠይቃለን።
4. በውጭም ሆነ በሐገር ውስጥ ያላችሁ የታሪክና የህግ ባለሙያ ወገኖች፣ የእነ ፕሮፌሰር አል ማሪያምን "HR 2003' ህገ ረቂቅ ፈለግ በመከተል፣ አግባብ በአለው ፍርድ ቤት የዚህን የክህደት ውል ህገ ወጥነት ለአለም እንድታጋልጡ ወገናዊ ጥሪያችንን እያቀረብን፣ በዚህም ጥረታችሁ የድጋፍ ድርጅታችን በሚችለው ሁሉ እንድሚተባበር ልናረጋግጥላችሁ እንወዳለን።
5. በየሐገሩ የምትገኙ የቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶችም ሆናችሁ ለዴሞክራሲና ለአንድነት የምትታገሉ ወገኖች በየ አላችሁበት ሐገር፣ ልሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች የጉዳዩን አሳሳቢነት በጹሁፍም ሆነ በአካል በመገኘት እንድታስረዱ ወገናዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

6. በመጨረሻም ዛሬ በሐገራችን መለስ ዜናዊና ተከታዮቹ የሚያደርሱትን ብሄራዊ ውርደት የመጀመሪያው አይደለም፣ የመጨረሻውም አይሆንም። በተለያዩ ደረጃ የተከሰተውን ችግር ለመርዳታ የምናደርገው ርብርቦሽ እንዳለ ሆኖ፣ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ዘላቂ መፍትሄ የሚገኘው፣ ዘረኛውና አምባገነኑን የመለስ ዜናዊ ቡድን ከሥልጣን በማስወገድ ስለሆነ፣ ዘረኝነትን በበሄራዊ አንድነት ፣ አምባገነንነትን በዴሞክራሲያዊ ሥርአት፣ ለመተካት በሚደረገው ትግል ውስጥ ሌሎች ልዩነቶችን አቻችሎ በጋራ መታገል የማይቻልበት ምንም ምክንያት ስለማይኖር፣ ለዚሁ ትግል በጋራ እንድትሰባሰቡ ወገናዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ዘረኝነት በብሄራዊ አንድንት ይተካል!!!
አምባገነንነት በዲሞክራሲያዊ ሥር አት ያከትማል!!!
ብሄራዊ ደህንንትና ጥቅም በአንድነትና በዴሞክራሲ ይረጋገጣል!!!

የቅንጅት ድጋፍ ስጭ ድርጅት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፤
ለንደን፣



1Crowndale Road London NW1 1TU Tel/Fax: 020 7168 9893 E-mail: kinijit97@yahoo.co.uk